# አርበኞች ግንቦት 7 የመከፋፈልና የመበተን አደጋ እንደገጠመው ሊቀመንበሩ ለደጋፊዎቹ በይፋ አረጋገጠ!!

የአርበኞች ግንቦት 7 የኤርትራው ጉባኤ የተሳካ እንደነበር የድርጅቱ አመራሮች ለሚደያ የተለያየ የሃሰት መግለጫ ሲሰጡ የሰነበቱ ቢሆንም የአርበኞች ግንቦት 7 ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሻዕቢያ ባለስልጣኖች በተገኙበት ከተለያዩ ሃገራት ለሰበሰባቸው ደጋፊዎቹ ብቻ አስመራ ከተማ በህግደፍ ጽ/ቤት ውስጥ ነሐሴ 30 ቀን 2009 ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ላይ ባካሄደው የመጀመሪያው ዝግ ስብሰባ ድርጅቱ ከፍተኛ የሆነ የመከፋፈል አደጋ እንደገጠመውና የነበረው ጥቂት ሰራዊትም እየተበተነ መሆኑን በማመን ለደጋፊዎቹ የይስሙላ ይቅርታ መጠየቁ ታውቋል፡፡

ይህ የመጀመሪያው ስብሰባ በድርጅቱ ሊቀመንበር በዶ/ር ብርሃኑ የተመራ ሲሆን በስብሰባው ላይ ከተለያዩ ሃገራት ከመጡት የብርሃኑ ደጋፊዎች በተጨማሪ ግርማቸው የተባለው እና ሌሎች ኤርትራ የቆዩ ጥቂት የብርሃኑ ደጋፊዎችን ሚካኤል የተባለ የሻዕቢያ ተወካይ ከአጃቢዎቹ ጋር የተገኙ ሲሆን የድርጅቱ አመራር የነበሩት መአዛው ጌጡ፣ አሰፋ ማሩ (አመነሸዋ) እና ኑርጃባ አሰፋ ያልተገኙበት ስብሰባ ነበር ፡፡

የድርጅቱ ሊቀመንበር ብርሃኑ ነጋ በዚህ ስብሰባ ላይ ያለፉት ሁለት ዓመታት ጉዞን በተመለከተ ለተሰበሰቡት ደጋፊዎቹ በሰጠው ማብራሪያ፡-

- በእነ መአዛው ጌጡ የሚመራ አንጃ ተፈጥሮ ድርጅቱ ለሁለት እንደተከፈለ፣
- ጥንስሱ በኢንተርኔት አንመራም የሚል አቋም ሲያራምድ በነበረው በዘመነ ካሴ መጀመሩንና በውጭ ሀገር የሚገኙ የአርበኞች ግንቦት 7 አባላት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ መከፈላቸውን፣
- ይህ የአርበኞች ግንባር አንጃ ብርሃኑ ነጋ አይመራንም የግንቦት 7 ተፅእኖ አንቀበለም የሚል አቋም በማንፀባረቅ ላይ እንደሚገኝ፣
- ችግሩን በተለያየ ጊዜ በሽምግልና ለመፍታት ጥረት ቢደረግም ሳይሳካ መቅረቱን፤
- አንጃው በፈጠረው ችግር ሠራዊቱ በቡድንና በግል ወደተለያዩ አካባቢ መበተኑን እና ይህንንም ለማስተካከል የኤርትራ መንግሥት ባደረገው ድጋፍ ከቀሩት በጣም በጣት የሚቆጠሩ የሠራዊት አባላት ጋር ግምገማ መደረጉን፣ በግምገማውም
    - መአዛው ጌጡ ስልጣኑን ከብርሃኑ ነጋ ለመቀማት ያሴር እንደነበር ማመኑን፣
    - አሰፋ ማሩ (አመነሸዋ) እና ኑርጀባ የሚዋዥቅ አቋም እንደነበራቸው፣
    - አንድ አመራር ሊጠፋ ሲል በመያዙ እስከ አሁን መታሰሩን ገልጿል፡፡ (ይህ ግለሰብ በሻዕቢያ በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ህይወቱ በአደጋ ላይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡)
- ግምገማውን ተከትሎ ጉባዔ እንዲጠራ መወሰኑን፣ አንጃው ጉባዔው እንዳይሳካ የተለያዩ ሙከራዎች ቢያደርግም በሻዕቢያ ሙሉ ትብብርና ድጋፍ ለጉባዔው እለት መደረሱን ፣

- በዚህ ጉባዔ ላይ ከሠራዊቱ ውስጥ 50 የማይሞሉ አባላት እንደሚሳተፉ እነርሱም በአንጃው የተለያየ በደል (እስር፣ ግርፋት፣ ከባድ የጉልበት ሥራ ......) የደረሰባቸው በመሆኑ የተነሳቀሉ መሆኑን፣

- ከአንጃው ጋር ትብብር ያደርጉ የነበሩት ሌሎች የአመራርና የሰራዊት አባላት በጉባዔው እንደማይሳተፉና ሐሬና ላይ ለብቻ ተነጥለው እንደሚገኙ (ታስረዋል ለማለት አልተፈለገም)፣

- መአዛው ጌጡ እና ቡድኑ ዘራፊና በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተሳታፊ መሆኑን ለዚህ የኤርትራ መንግሥት የተደበቁ በርካታ መሣሪያዎችና ገንዘብ እንዳገኘባቸውና በምርመራ ላይ መሆኑን በመወንጀል፣

የዚህ ሁሉ ችግር ዋና መነሻው የተበላሸ የአሰራር ባህልና ልምድ ካለው ጋር ራሱን የአማራ ወኪል ነኝ ከሚለው የሽፍቶች ስብስብ ከሆነው የአርበኞች ግንባር ጋር የተደረገው ውህደትና ውህደቱን ተከትሎ የአመራር ቦታ በአቅም ሳይሆን በኮታ መደልደሉ መሆኑን የገለፀው ብርሃኑ ነጋ በዚህ ለፈፀምነው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን በማለት መሬት ላይ በሌለ የሃሰት ወሬ ሲነዱ የከረሙት ከተለያዩ ሃገራት ወደ አስመራ የገቡት የድርጅቱ አባላት ኤርትራ ውስጥ በሚያጋጥማቸው ያልጠበቁት ሁኔታ እንዳይደናገጡ ከወዲሁ ለማረጋጋት ጥረት በማድረግ ለጉባኤው እንዲዘጋጁ ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይቀጥላል.....